**ለክቡር ዶ/ር ኢያሱ አብረሃ**

**በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ**

**ለእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር ሚኒስትር**

**<u>አዲስ አበባ</u>**

**ጉዳዩ:- <u>የግብርና ትራንስፎርሜሽን ኤጀንሲን የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ሪፖርት ይመለከታል</u>፤**

በርዕሱ የተጠቀሰውን ኤጀንሲ የኦዲት ውጤትና አስተያየት የያዘ 5 ገጽ የኦዲት ሪፖርት እና 7 ገጽ የሂሣብ መግለጫዎች በድምሩ 12 ገጽ ከዚህ ደብዳቤ ጋር አያይዘን የላክን መሆኑን እንገልጻለን፡ ፡

ከማክበር ሰላምታ ጋር!

ሰለሞን መብራቱ

የልማትና ማኅበራዊ መሥሪያ ቤቶች

ኦዲት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር

**<u>ግልባጭ</u>፡ -**

ለግብርና ትራንስፎርሜሽን ኤጀንሲ (ከ12 ገጽ አባሪ ጋር)

**<u>አዲስ አበባ</u>**

ለተወካዮች ምክር ቤት የተላከው የሂሳብ መግለጫዎችን አይጨምርም፡፡

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ

## በእርሻና ተፈጥሮ ሃብት ሚኒስቴር

## የግብርና ትራንስፎርሜሽን ኤጀንሲ

# የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ

# ኦዲት ሪፖርት

መጋቢት 2010 ዓ.ም

አዲስ አበባ

<u>በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ</u>

<u>በእርሻና ተፈጥሮ ሃብት ሚኒስቴር</u>

<u>የግብርና ትራንስፎርሜሽን ኤጀንሲ</u>

<u>የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ሪፖርት</u>

የግብርና ትራንስፎርሜሽን ኤጀንሲ የተመደበለትን የመደበኛ በጀት በፋይናንስ አዋጁ፣ ደንቡ እና በተከታታይ በወጡ መመሪያዎች መሰረት ለታቀደለት ዓላማ ማዋሉን፤ እንዲሁም ሂሳቡ በመንግሥት የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሰረት መያዙንና የመንግሥት ሃብትና ንብረት በሚገባ መጠበቁን ለማረጋገጥ ከዚህ ሪፖርት ጋር የተያያዙትን የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ሪፖርቶችን እና የሂሳብ ማስታወሻዎችን ኦዲት አድርገናል።

የሂሳብ ሪፖርቶችን የማዘጋጀት ኃላፊነት የግብርና ትራንስፎርሜሽን ኤጀንሲ ሥራ አመራር ሲሆን፣ የሂሳብ ሪፖርቶችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት ኃላፊነት ነው።

ኦዲቱ የተከናወነው የፌዴራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመሥሪያ ቤታችን በተሰጠው ሥልጣን መሠረት የዓለም አቀፍ ኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI) መሠረት በማድረግና የዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤትን የኦዲት ሥልት በመከተል ነው።

እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ላይ አጥጋቢ የሆነ ማረጋገጫ (የኦዲት አስተያየት) ለመስጠት ያስችለናል።

ከዚህም በተጨማሪ ኦዲቱ የተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ ደንቦች እና በተከታታይ የወጡ መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆኑን በናሙና ኦዲት ማከናወንን ይይዛል።

የሂሳብ መግለጫዎች ጉልህ ከሆኑ መዛባቶች የፀዱ ለመሆኑ በቂ ማስረጃ፣ አጥጋቢ ማረጋገጫና ማብራሪያ ሊያስገኝ በሚችል መልኩ ኦዲቱን አቅደን አከናውነናል። አስተያየት ላይ ለመድረስ በሂሳብ መግለጫዎች ላይ ያለውን የመረጃ አቀራረብ አጠቃላይ ብቃት ገምግመናል። ይሁን እንጂ በሪፖርቱ ላይ ከተመለከቱት የአሰራርም ይሁን የሂሳብ አያያዝ ድክመቶች በተጨማሪ ሌሎች ድክመቶች ወይም ስህተቶች ሊኖሩ የሚችሉ ከመሆኑም በላይ የሂሳብ መግለጫውን

ለማዘጋጀት የተዘረጉትን  የውስጥ ቁጥጥርና ሌሎች  ድክመቶችን ሙሉ በሙሉ ሊያሳይ አይችልም። ለኦዲቱ ሥራ መሰረት የሆኑት ኤጀንሲው ያቀረባቸው የሂሳብ መግለጫዎች፣ መዛግብት፣ ደጋፊ ማስረጃዎች እንዲሁም በኤጀንሲው ሥራ አመራር የተሰጡ ማብራሪያዎች ናቸው።

ኦዲቱ የተከናወነው የበጀት ዓመቱን የሂሳብ እንቅስቃሴ ሊወክሉ የሚችሉ ናሙናዎችን ወስዶ በጥልቀትና በዝርዝር ኦዲት በማድረግ ነው።

የሚከተሉት በኤጀንሲው የተዘጋጁ የሂሳብ መግለጫዎች፡ -

- የሂሳብ ማመዛዘኛ፣
- የገቢ ሂሳብ ሪፖርት፣
- የመደበኛ ወጪ ሂሳብ ሪፖርት፣
- የተሰብሳቢ ሂሳብ ሪፖርት፣
- የተከፋይ ሂሳብ ሪፖርት፣
- የዝውውር ሂሳብ ሪፖርት፣

ከዚህ የኦዲት ሪፖርት ጋር ተያይዘው ቀርበዋል።

የግብርና ትራንስፎርሜሽን ኤጀንሲ የ2009 የሂሣብ መግለጫዎች ጉልህ የሆነ ግድፈት የሌለባቸው፣ በአዋጅ በተፈቀደው በጀት በመንግሥት የሂሣብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት በትክክል የተዘጋጁና፣ የተከፈለው ወጪና የበጀት አጠቃቀሙ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅን፣ ደንብና መመሪያን ጠብቆ የተከናወነ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

1. ሰኔ 2004 በወጣው የመንግሥት ሠራተኞች የቀን ውሎ አበል አከፋፈል መመሪያ አንቀጽ 3 መሰረት አንድ የመንግሥት ሠራተኛ ከመደበኛ የሥራ ቦታው ውጪ ወደ ሌላ የሥራ ቦታ ለሥራ ጉዳይ ሄዶ እለቱን መመለስ  ካልቻለ ለቁርስ፣ ለምሳ፣ ለእራትና ለአልጋ በሰራተኛው የደመወዝ መጠን ልክ በወጣው የውሎ አበል ተመን መሰረት ክፍያ የሚፈጸም መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ከወሎ አበል አከፋፍል ተመን በላይ ክፍያ በመፈጸሙ ምክንያት፡-

    1.1. ኤጀንሲው ለሰራተኞቹ ብር 10,690.00 በውሎ አበል መመሪያው ከተፈቀደው በላይ የውሎ አበል ክፍያ እና ሌሎች ክፍያዎች ብር 49,780.75 በድምሩ ብር 60,470.75 የፈጸመ መሆኑ፣

1.2. ኤጀንሲው ከክልል ለመጡ ሰልጣኞች በውሎ አበል መመሪያው ከተፈቀደው በላይ የውሎ አበል ክፍያ ብር 2,214,257.80 እና ሌሎች ክፍያዎች ብር 9,713,700.00 በድምሩ ብር 11,927,957.80 የፈጸመ መሆኑ፣

1.3. ከመጡበት መሥሪያ ቤት (ቢሮ) መገጣጠሚያ ደብዳቤ ሳይኖራቸው ብር 339,184.44 የውሎ አበል ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ፣

1.4. የውሎ አበል ክፍያውን ለመቀበላቸው ሳይፈርሙ በወጪ የተመዘገበ ብር 11,956.00 የተገኘ መሆኑ፣

2. በሚኒስትሮች ምክር ቤት በወጣው የግብርና ትራንስፎርሜሽን ምክር ቤት እና የኤጀንሲ ማቋቋሚያ (ማሻሻያ) ደንብ ቁጥር 380/2010 አንቀጽ 5(ለ) ኤጀንሲው የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎች መሰረታዊ መርሆዎችን ተከትሎ በመንግሥት በሚጸድቅ መመሪያ መሰረት ሰራተኞችን እንደሚቀጥርና እንደሚያስተዳድር ተደንግጓል። ከዚህም በተጨማሪም የሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር ለጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት ሐምሌ 1 ቀን 2007 ዓ.ም በቁጥር ሲሰሚ13/ጠ48/46/1049 ባስተላለፈውና በጸደቀው የግብርና ትራንስፎርሜሽን ኤጀንሲ የሥራ መደቦች ደረጃ፣ የደመወዝ ስኬል እና የተፈላጊ ችሎታዎች መመሪያ መሰረት ክፍያ የተፈጸመ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ኤጀንሲው ከሐምሌ 1 ቀን 2009 ዓ.ም እስከ ታህሳስ 30 ቀን 2009 ዓ.ም ድረስ ባለው የስድስት ወር ጊዜ ውስጥ በሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር ከብር 3,499.00 ዝቅተኛው የደመወዝ ስኬል እስከ ከፍተኛው የደመወዝ ስኬል ብር 5,535.00 በተፈቀደው መሰረት ብር 1,351,701.00 መከፈል ሲገባው ባልተፈቀደ ዝቅተኛው የደመወዝ ስኬል ብር 15,539.00 እስከ ከፍተኛው የደመወዝ ስኬል ብር 50,035.00 ድረስ ብር 6,120,444.00 ክፍያ በመፈጸሙ ምክንያት ከተፈቀደው በላይ ብር 4,768,743.00 ክፍያ ፈጽሞ የተገኘ መሆኑ፤

3. በኤጀንሲው የሚፈጸሙ ክፍያዎች በሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር የተፈቀዱ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ኤጀንሲው ከሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር ፍቃድ ሳያገኝና ክፍያውን የሚደግፍ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ ሳይኖር ለኤጀንሲው ለተለያዩ ሰራተኞችና ለቤተሰቦቻቸው የጤና ኢንሹራንስ (Health Insurance) ብር 203,210.36፤ የግሩፕ የህይወት ዋስትና (Group Life Insurance) ብር 2,195,303.61 እንዲሁም ለገንዘብ ዋስትና (Money & Fedelity Guarantee) ብር 18,498.00 በድምሩ ብር 2,417,011.97 ለተለያዩ የኢንሹራንስ ድርጅቶች ክፍያ ፈጽሞ የተገኘ መሆኑ፤

4. በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 190/2002 አንቀጽ 32 እንዲሁም በፌዴራል የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 4/2003 መሰረት ለውሎ አበልና ለመጓጓዣ የተሰጠ ቅድሚያ ክፍያ ሰራተኛው ሥራውን አጠናቆ ከተመለሰ በኋላ፤ በመመሪያ ቁጥር 5/2003 መሰረት ደግሞ ለግዥ የተሰጠ ቅድሚያ ክፍያ በሰባት ቀናት ውስጥ መወራረድ እንዳለበት ያዛል። ኤጀንሲው በደንቡና በመመሪያው መሰረት የፈጸመ መሆኑ ሲጣራ በተሰብሳቢ በሂሳብ ኮዶ 4210 እና 4274 ከአንድ ወር አስከ አንድ ዓመት ድረስ የቆየ ብር 161,590.19 በደንቡ መሰረት ያልተወራረደ (ያልተሰበሰበ) መሆኑ፤

5. ኤጀንሲው የሚፈጽመው የውሎ አበል ክፍያ ሰኔ 2004 በወጣው የመንግሥት ሠራተኞች የቀን ውሎ አበል አከፋፈል መመሪያ መሰረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ኤጀንሲው በደሴ ከተማ ባካሄደው ስልጠና (ስብሰባ) ወቅት የውሎ አበል ክፍያ ሲፈጸም ክፍያ በተፈጸመበት ሰንጠረዥ ላይ ለአንድ ተሳታፊ የውሎ አበል ክፍያ ብር 672.00 እንዲሁም ለአኩሜዴሽን ተብሎ ብር 900.00 በድምሩ ብር 1,572.00 ክፍያ የፈጸመ ሲሆን፣ ቢዚያው ክፍያ በተፈጸመበት ሰንጠረዥ ላይ ለተመሳሳይ ግለሰቡ ለተመሳሳይ ቀንና አገልግሎት ብር 1,572.00 በድጋሚ ክፍያ ፈጽሞ የተገኘ መሆኑ፤

ታውቋል።

ከላይ ከተራ ቁጥር 1 እስከ 5 በዝርዝር በተገለጹት ምክንያቶች በእኛ አስተያየት የግብርና ትራንስፎርሜሽን ኤጀንሲ የሂሣብ መግለጫዎች በበጀት ዓመቱ እስከ ሰኔ 30 ቀን 2009 ዓ.ም ድረስ የተሰበሰበውን ገቢ የተፈፀመውን ወጪና የበጀት አጠቃቀሙን በአጥጋቢ ሁኔታ አያሳዩም።

ምንም እንኳ ከላይ የተሰጠውን የኦዲት አስተያየት የማይቀይረው ቢሆንም፣ ቀጥሎ የተመለከቱት ጉዳዮች ትኩረት ሊሰጣቸው፣ እርምጃ ሊወሰድባቸው እና ለወደፊቱም ጥንቃቄ ሊደረግባቸው ይገባል።

1. **<u>ትኩረት ሊሰጥባቸው የሚገባቸው ጉዳዮች (Emphasis of Matters)</u>**

   ለኤጀንሲው በ2009 በጀት ዓመት በየፕሮግራሞቹ የተፈቀደው የወጪ በጀት አጠቃቀም ሲታይ ከመደበኛ በጀት በየሂሳብ ኮዶቹ ከ10% በላይ ብር 21,534,262.98 ሥራ ላይ ያልዋለ መሆኑ ታውቋል።

## 2. **<u>ልዩ ልዩ ጉዳዮች (Other Matters)</u>**

**2.1.** በፌዴራል መንግሥት የንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 መሰረት የስቶክ መዛግብቶች የመያዝና ስቶክ የመረከብ እንዲሁም ወጪ የማድረግ ኃላፊነቶች ለአንድ ሰራተኛ መሰጠት እንደሌለባቸው ተመልክቷል። ይሁን እንጂ ስቶክ የመያዝ፣ ስቶክ የመረከብ እንዲሁም ወጪ የማድረግ ኃላፊነቶች በአንድ ሰራተኛ የሚከናወን መሆኑ፤

**2.2.** በፋይናንስ አዋጅ ቁጥር 648/2001 እና በፋይናንስ አዋጅ ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 970/2008 እና አዋጁን ለማስፈጸም በወጣው መመሪያ ቁጥር 47/2009 መሰረት እንዲሁም በሚኒስትሮች ደንብ ቁጥር 190/2002 አንቀጽ 61 ንዑስ አንቀጽ 3 መሰረት እያንዳንዱ የመንግሥት መሥሪያ ቤት የዉስጥ ኦዲት ክፍል በየሩብ አመቱ የመሥሪያ ቤቱ ሥራ አመራርና ሠራተኞች ኃላፊነታቸዉን በብቃት መወጣት እንዲችሉ በተዘረጋዉ የዉስጥ ቁጥጥር ሥርዓት በሥራ ላይ ባሉት ህጎችና የአሰራር ሥርዓቶች መሰረት ስራዎች መከናወናቸዉን ኦዲት እያደረገ በመመሪያዉ ላይ በተቀመጡት ግዜ ዉስጥ ለመሥሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊና ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ሪፖርት የሚያደርግ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ የኤጀንሲው የውስጥ ኦዲት ክፍል የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ያላደረገ መሆኑ፤

ታውቋል።

የፌዴራል ዋናው ኦዲተር መሥሪያ ቤት

መጋቢት 2010 ዓ.ም